# አጀንዳዎች

1. የእስልምናን ምንነት መረዳት
2. እስልምና በክርስትና መሰረታዊ ትምህርት ላይ የሚያነሳቸው ቁርዓናዊ ትችቶች መረዳት
   - የትምህርተ ስላሴ ተዓማኒነት
   - የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነት እና አምላክነት
   - የመጽሀፍ ቅዱስ ተዓማኒነት
3. የመለኮታዊ መጽሐፍ ቁርአናዊ መለኪያዎች
4. በመጽሀፍ ቅዱስ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችን እንዴት እንመልስ?
5. በተመረጡ ጥያቄዎች ላይ መወያየት

# ኢስላም ምንድን ነው?

# ቁርዓን ምን ይላል

إِنَّ **<u>الدِّينَ</u> عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ** ۗ وَمَا اخْتَلَفَ الَّذِينَ أُوتُوا الْكِتَابَ إِلَّا مِن بَعْدِ مَا جَاءَهُمُ الْعِلْمُ بَغْيًا بَيْنَهُمْ ۗ وَمَن يَكْفُرْ بِآيَاتِ اللَّهِ فَإِنَّ اللَّهَ سَرِيعُ الْحِسَابِ [٣:١٩]

አላህ ዘንድ (የተወደደ) **<u>ሃይማኖት</u>** ኢስላም ብቻ ነው፡፡ እነዚያም መጽሐፉን የተሰጡት ሰዎች በመካከላቸው ላለው ምቀኝነት ዕውቀቱ ከመጣላቸው በኋላ እንጅ አልተለያዩም፡፡ በአላህም አንቀጾች የሚክድ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው፡፡

**ሱረቱል አሊ-ዒምራን 3 ፡ 19**

# የኢስላም ሊቃውንት ምን ይላሉ?

**አምና ፋሩቅ፡-**

"ኢስላም **ዲን እንጂ ሃይማኖት** አይደለም፡፡“ (A DEEN NOT MERE RELIGION, THE DIALOGUE VOLUME IV NUMBER 1, WWW.QURTUBA.EDU.PK/THEDIALOGUE, PAGE 97)

**ዶ/ር ተንቪር ሁሳይን**

"አል-ኢስላም **አድ-ዲን እንጂ ማዝሃብ (ሃይማኖት)** አይደለም፡፡ ማዝሃብ የሚለው ቃል በቁርአን አልተጠቀሰም፡፡“ (HTTP://QURANICTEACHINGS.ORG/DEEN/)

# በዲን እና በሃይማኖት (ማዝሃብ) መካከል ያለ ልዩነት፡-

- ‘ማዝሃብ’ (RELIGION) (ሃይማኖት) የሚለው ቃል የመጣው ‘ዛሃብ’ ከሚል ስርዎ ቃል ነው፤ ይህ **መሔድ፣ ማለፍ** ወይም **መራመድ** ማለት ነው፡፡ **የሃይማኖት የቃል በቃል ትርጉሙ እምነት፣ አጉል ልምድ ማለት ነው፡፡** የላቲን ቃል ነው፤ RELIGION (ሃይማኖት) ማለት **በአንድ ላይ ማሰር ማለት ነው፡፡** RELIGION (ሃይማኖት) በሃይማኖት ተከታዩና በእርሱ አምላክ መካከል ያለ መተሳሰር ነው፡፡ ይሄ የሃይማኖት ታማኝነት በሃይማኖታዊ ባዓላትና በእምነት ሁሉ ነው፡፡

- **‘ዲን’ ግን የተሟላ ስርዓት ነው**፤ በኢስላም ጉዳይ የአላህን ፍጹም ሉአላዊነት መቀበል ማለት ነው፡፡ ይሄም ፍጹም ሉአላዊ ለሆነው የሰው ፍጹም መገዛት ነው፡፡ ዲን ብድራትንና ተጠያቂነትን የሚጠቀልል፣ **በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካና በሃይማኖታዊ ስርአት የሚሠራ የተሟላ የሕይወት ደንብ ነው፡፡** ‘ዲን’ መለኮታዊና እንዲሁም ታታሪ ነው፡፡ ‘ዲን’ የተቋማት፣ የማህበራዊ ስርአት፣ የልምዶችና የእምነት ስብስብ ነው፡፡ **ኢስላም ዲን እንጂ ሃይማኖት አይደለም፡፡** (**HTTPS://WWW.ALQURANCLASSES.COM/DIFFERENCE-BETWEEN-DEEN-AND-RELIGION**)

# የተሟላ የሕይወት ደንብ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

- እስልምና ከክርስትና፣ ከአይሁድና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር በንጽጽር ሲታይ ሃይማኖት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም እስልምና የሰዎችን ሕይወት **የሚመራ 'ብቸኛና' ሁሉን የሚጠቀልል የፖለቲካ ጽንሰ ሐሳብ /IDEOLOGY/ ነው፡፡** እንደ ሌሎቹ 'የፖለቲካ ጽንሰ ሐሳቦች' /IDEOLOGY/ እስልምና አስተምህሮ፣ ደንቦችና የቁጥጥር ሥርዓቶች አሉት፡፡ ነገር ግን ከሌሎቹ የሚለየው ሰው ሰራሽ ባለመሆኑ ነው፡፡ **/RISALA PUBLICATIONS/**
- **ኢስላም 'ዲን' እንጂ 'ሃይማኖት' አይደለም** ሲባል ጥያቄ ይነሳል፡፡ ኢስላም **ካፒታሊስታዊም ኮሚኒስታዊም** ያልሆነ ልዩ የኢኮኖሚ ስርዓት አለው፡፡ ኢስላም ከዘመናዊው ወለድን መሰረት ካደረገ የባንክ ስርአት ጋር የማይመሳሰል **'ኢሽትራአክ'** የተባለውን ያስተዋውቃል፡፡ ይሄ አስተሳሰብ በሁለቱ **የፖለቲካ ጽንሰ ሐሳቦች /IDEOLOGY/** መካከል አንዴ ቦግ ሌላ ጊዜ ጥፍት ለሚለው ጦርነትና ዘወትር ለሚወድቀው ኢኮኖሚ መቋጫ ያስቀምጥለታል፡፡ በተጨማሪ ኢስላም አገዛዝና አስተዳደር ላይ የተሟላ መመሪያን ያቀርባል፡፡ **ኢስላም በዴሞክራሲና በንጉሣዊ አገዛዝ መካከል ያለም የአገዛዝ ስርአት ያቀርባል፤ በሁለቱ አገዛዞች ያለን ጉድለት ያስወግዳል**፡፡ እንዲሁም የተወሰኑ ብቸኛ ኢስላማዊ ጽንሰ ሐሳቦችን ይጨምራል፡፡ በሕዝብ አስተዳደር ላይ ግልጽ መመሪያዎች አሉት፡፡ አልፎ ተርፎም **ስለ ውጊያ ህግጋቶች ያስተምራል**፣ ተዋጊ ያልሆኑትን እንክብካቤን፣ የጦር ስልትን ያስተምራል፡፡ **ነጻነትን መሰረት ካደረገው የምእራባውያን ስርዓት ጋር አይመሳሰልም፡፡** ኢስላም የሚሰጠው በወንድማማችነት ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ስርአት ነው፡፡ **(ዶ/ር ኸሊፋ አብዱል ሐኪም 'ISLAMIC IDEOLOGY')**

# በዚህ ውስጥ የሙስሊሙ ስነምግባር በምን ይገለጻል?

"**የሙስሊም ስነምግባር ፖለቲካዊ ስነምግባር ነው፤** የተሳሳተ ትርጉም ካልተሰጠው ወይንም በተሳሳተ መንገድ ጥቅም ላይ ካልዋለ በስተቀር፣ የሙስሊም ስነ ምግባር በእምነት፣ በሸሪአ፣ በአምልኮና በትምህርት የተገነባ ፖለቲካዊ ስነምግባር እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡

**ፕሮፌሰር ዩሱፍ አል-ቃራዷዊ**

# በዚህ የፖለቲካ እሳቤ የማህበረሰብ ተሳስሮ ምን መሆን አለበት

አንድ መስሊም ላኢላህ ኢለላይ ስላለ ብቻ መስሊም ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከኢስላም ውጪ ካሉት መለየት ጠላትነቱን ማወጅ ጠላትነቱን ግልጽ ማድረግ አለበት፡፡ ከእነሱ በቀል ይደርስብኛል ብሎ ካሰበ ግን ይሄንን ሊደብቅ ይችላል፡፡

አልወላ ዋልበራ

ይሄ አስተምህሮ ተቂያህ ሲባል በነቢዩ መሀመድ ዘመን በስፋት ሲተገበር የነበረ ልምድ ነበር፡፡ የኢስልምናን እውነተኛ ማንነት እንዳይታወቅ ለዘመናት ያገዘ አካሄድም ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ የኢስልምና አካሄድ ከአካባቢ አካባቢ እንዲለያይ ያደረገ ሲሆን ከኢስላም ውጪ ያሉት እውነተኛ ባህሪውን እንዳያውቁ አድርጎዋል

# የኢስላም ሁለት ገጽታዎች እና መቆሚያዎቹ



# ነብዩ መሐመድ ብቸኛ መንግስት ለመሆን ምን አደረገ?

- **ዶ/ር ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ ኢስላምን መረዳት በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዲህ አሉ፡-**

"የኢስላምን ታሪክ ስንመለከት የአላህ መልእክተኛ በቻሉት የማሰብ ክህሎትና ጉልበት ሁሉ ተጠቅመው፣ በወሕይ አመራር በመታገዝ ኢስላማዊውን መንግስት ለመመስረት፣ ለደዕዋቸው አገር፣ ለሙስሊሞች ማረፊያ ቦታ፣ ከአላህ ሸሪዓ ውጭ ሌላ ተቀናቃኝ ስልጣን የሌለበት ምድር ለማግኘት ሠርተዋል፡፡ ይህ በመሆኑም ልዩ ልዩ ጎሳዎችን በርሳቸው እንዲያምኑና እንዲያስጠጓቸው፣ ከጥቃትም እንዲታደጓቸውና ጥላ ከለላ እንዲሆኑላቸው ጠይቀዋል፡፡

አላህ ለዚህ ተግባር አንሷሮችን አነሳሳ፡፡ አውስና ኸዝርጅ የተባሉ ጎሣዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጎሳዎች በነቢዩ መልእክት አመኑ፡፡ በውስጣቸው ኢስላም ተስፋፋ፡፡ 73 ወንዶችንና ሁለት ሴቶችን ያካተተ ልዑክ ወደ ሐጅ ላኩ፡፡ ከጠላት ጥቃት፣ ልክ ባለቤቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውንና ራሳቸውን እንደሚከላከሉት እርሳቸውንም ሊከላከሉ፣ ሊታዘዟቸው፣ በመልካም ሊያዙና ከመጥፎ ሊከለክሉ ወዘተ... ቃል ገቡ፡፡ **ወደ መዲና የተደረገው ስደት ልዩ በሆነ ኢስላማዊ መንግሥት የሚመራ ኢስላማዊ ሕብረተሰብ የመመስረት ጥረት ዋነኛ አካል እንጂ ሌላ አይደለም፡፡**

# የቀጠለ...........

- እናም መዲና የኢስላም አገር፣ የአዲሱ ኢስላማዊ መንግሥት መሠረት ሆነች፡፡ መንግሥቱ የሚመራው በነቢዩ ሙሐመድ ነበር፡፡ እርሳቸው የሙስሊሞች ነቢይ እና መልእክተኛ እንደሆኑ ሁሉ ንጉሣቸውም ሆኑ ይህን **መንግሥት ለማጠናከር፣ በጥላው ተጠልሎ ለመኖር እና በአርማው ስር መዋጋት በጊዜው ኢስላምን በተቀበሉ ሁሉ ላይ ሃይኖታዊ ግዴታ ተደረገ"**

**ዶ/ር ዩሱፍ አል-ቀረዷዊ ኢስላምን መረዳት**

# የመወያያ ጥያቄ

በሀገራችን እንዲሁም በአለም የመንግስታት ታሪክ ውስጥ ክርስትና እና የመንግስት መዋቅር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የክርስትና እምነት ከመንግስት ጋር የነበረው ግንኙነት እስልምና ከመንግስት ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር ሲታይ አንድ አይነት አያደርገውም?

# ታዲያ ምን እናድርግ

- የኢስልምናን ዘመን ተሻጋሪ ሁሉን አቀፍ ተገዳዳሪነት መረዳት
- ኢስልምና እኛ ዝም ብንለው እንኩዋን ዝም ሊለን እንደማይችል መረዳት
- በተከታዮቹ መካከል የአካሄድ እንጂ የግብ ልዩነት እንደሌለ ማወቅ
- የኢስልምና ሁለት ገጽታዎች እንዴት ተደጋግፈው እንደሚሄዱ ጠንቅቆ ማወቅ
- ኢስላም ሂደታዊ እንደሆነ ማወቅ እንዲሁም
    - ከክርስትና በተለየ እንደወቅቱ ተለዋዋጭ በሆነ ሂደት የሚሄድ
- እያንዳንዱ አካሄዱ የተቂያህ ትምህርቱ ላይ የተመሰረተ መሆኑን መረዳት